# የወያኔ/ኢሕአዴግ የጥፋት ልዑካን ሕዝብ እያደናገሩ ነው፤

## ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ

## ማሳሰቢያ

ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ. ም.
June 25, 2008

ወያኔ/ኢሕአዴግ በድብቅ ፈርሞ ለሱዳን በሰጠው መሬትና በፈጸመው የሀገር ክህደት ሴራ በይፋ ከተጋለጠበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞ እየገጠመው ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቀውና ሳይመክርበት በድብቅ ለባዕድ አሳልፎ ሲሰጥ እጅ ከፍንጅ ተይዞ የተጋለጠ መንግሥት ጥፋቱን አምኖ የድብቅ ውሉንም መሠረዝና የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ ሲገባው፤ ጉዳዩን ለመሸፋፈን ሲል ሌላ ደባና ወንጀል በመፈጸም ላይ ነው።

ባለፈው ወር የሰጠው የተምታታ አሉታዊ ማስተባበያው የተፈጥሮ ባሕሪውን በበለጠ በማጋለጥ ከባሰ ማጥ እያገባው መሆኑ እየታወቀ፤ ሰሞኑን ደግሞ ያዋጣኛል ብሎ የጀመረው አዲስ የማሳሳቻ ተንኮል፤

1ኛ በአንድ በኩል መሬቱን ማሳረከቡ እየታወቀ የተፈናቀሉ ገበሬዎቹን ዓይን ባወጣ መሰሪነት መሬታችሁን እረሱ እያለ ጊዜ ለመግዛት እየተሯሯጠ ሲገኝ፤ በሌላ በኩል ለድንበራቸው እንደነ አፄ ዮሐንስ እንሰዋለን ብለው የተነሱትን ወገኖቻችን በማሸበር ላይ ይገኛል።

2ኛ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን በጥቅማ ጥቅም ደልሎ የሀገር ክህደት ተባባሪ ለማድረግ የአማራ ክልል ብሎ በሚጠራቸው ካድሬዎቹና የሀገራቸውን ክብር በግል ጥቅም በለወጡ ግለሰቦች አማካይነት መሬት እንሰጣችኋለን፣ ቤት በርካሽ ዋጋ እንሸጥላችኋለን፣ ሌላም ሌላ ጥቅም እናደርግላችኋለን እያለ የውጪን ኢትዮጵያዊ ለመደለል በሰሜን አሜሪካ ከተሞች ዘመቻ ጀምሯል።

በ2ኛው ቁጥር በተመለከተው ዓላማው መሠረት ባለፈው እሑድ (June 22, 2008) ኅሊና ቢስ የሆኑና ለሆዳቸው ያደሩ የመለስ ዜናዊ የክህደት መልዕክተኞች በዳላስ ከተማ ሲያምታቱ፤ ለወገናቸውና ለሀገራቸው ተቆርቋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ፊት ለፊት በመጋፈጥ አሳፍረው መልሰዋቸዋል። ሐፍረት ለምኔ ያሉት እነዚህ ካድሬዎች ግን በሚቀጥሉት ሳምንታት በሌሎች የአሜሪካ ከተሞች ለመዶለት በግልና በይፋ ጥሪ በማቅረብ ፕሮግራማቸውን በመበተን ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ለወያኔ ተባባሪ የሆኑ ለጥቅም ያደሩ ካድሬዎችና ተባባሪ ስግብግቦች በሚዶሉቱበት ቦታ ሁሉ ተከታትሎ በተቻለው መጠን እንዲያጋልጣቸው ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በልጆቿ ይከበራል
ኢትዮጵያ በክብሯ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
e-mail: ethiosudanborder@yahoo.com